# የቼክ ምንነት በኢትዮጵያ ህግ



በዮሐንስ ግርማ(LLB,LLM)

2015 ዓ/ም

## መግቢያ

በዚህ አጭር ፅሁፍ በሀገራችን የንግድ እንቅስቃሴ በስፋት ጥቅም ላይ የሚውለውና ችግሮች ከሚስተዋሉባቸው ተላላፊ የገንዘብ ሰነዶች ወይም የንግድ ወረቀቶች አንዱ የሆነውን የቼክን ምንነት፣ ባህሪያት፣ አጠቃቀም፣ በቼክ ማጭበርበር የወንጀልና አስተዳደራዊ ተጠያቂነት ላይ ትኩረት በማድረግ ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡

## የቼክ ምንነት

የቼክን ምንነት በተመለከተ በአገራችን የንግድ ህግ ቀጥተኛ ትርጉም አልተሰጠውም፡፡ ነገር ግን ቼክ  የንግድ ወረቀት  ወይም ተላላፊ የገንዘብ ሰነድ መሆኑን ከህጉ የተለያዩ ድንጋጌዎች ጥምር ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ተላላፊ የገንዘብ ሰነድ ማለት በንግድ ህግ አንቀጽ 715 መሰረት መብቱ ከሰነዱ ተለይቶ ሊሰራበት ወይም ሊተላለፍ የማይችል ያገልግሎት መብት ያለበት ሰነድን በሙሉ የሚያካትት ሰነድ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በዚሁ ህግ አንቀጽ 732 መሰረት ቼክ በገንዘብ መከፈል የሚሆነውን ግዴታ የሚናገር ተላላፊ የገንዘብ ሰነድ ነው፡፡ ቼክ በአውጪው የተገለጸው መብት ከዚሁ ሰነድ ተለይቶ ሊሰራበት የማይችል ያለሰነዱ መብቱ የማይተላለፍ ልዩ ተላላፊ የንግድ ወረቀት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በቼክ ለተገለጹ የህግ ግዴታዎች የሚገደደው ህጋዊ ውጤት ያላቸውን ተግባራት ለመፈጸም  በህግ ችሎታ ያለው ሰው ነው፡፡ ቼክ ለተፋጠነ፣ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና አስተማማኝ ለሆነ የፋይናንስ ግብይት አመቺ የሆነ መሣሪያ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በተለይም ጥሬ ገንዘብ መያዝ ሳያስፈልግ ግብይቶችን ወይም ማንኛውንም ክፍያዎችን ለማከናወን እና ውጤታማ የግብይት ስርአት ለመፍጠር ጠቃሚ ነው፡፡ ከኤሌክትሮኒክ ክፍያ ስርአት አንጻር  ሲታይ በዚይ ልክ ፈጣንና ቀልታፋ ነው ባይባልም የራሱ የሆነ መልካም ጎኖች አሉት እነሱም ገንዘብን ከማንቀሳቀስ አንጻር በቼክ የሚፈጸም የክፍያ ሂደት ቀልጣፋ እና ፈጣን ነው ሊባል ይችላል፡፡ በተጨማሪም በሰነድ የሚተላለፍ በመሆኑ ከማጭበርበር እና መሰል ድርጊቶች ለመከላከል ይረዳል፡፡ በአገራችንም በቼክ የመጠቀም ልምድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመምጣቱን ያህል ከቼክ ጋር የተያያዙ ችግሮችም እንዲሁ እራሳቸውን እያወሳሰቡ መጥተዋል፡፡

በ1952ቱ የንግድ ህግ አንቀጽ 827 መሰረት አንድ ቼክ ሊያሟላ የሚገባው የፎርም ይዘት፡-

- ✓ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ቅድመ ሁኔታ /ሐተታ/ ያልተደረገበት ትዕዛዝ፣
- ✓ መክፈል ያለበትን /የሚገባውን/ ከፋይ ስም፣
- ✓ ገንዘብ የሚከፈልበትን ቦታ፣
- ✓ ቼኩ የወጣበት ቦታና ጊዜ፣
- ✓ ቼኩን ያወጣው ሰው ፊርማ መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

በቼክ እንዲከፍል የሚታዘዝ ሰው ክፍያውን እንዲፈጽም የሚገደደው በባንክ ወይም በህግ እንደ ባንክ በታወቀ ስራ ማስኬጃ መስሪያ ቤት ሊሆን እንደሚገባ የንግድ ህጉ በአንቀጽ 829 ያመለክታል፡፡ ይህም ማለት በቼክ ክፍያ የሚያዝ ሰው ክፍያው እንዲፈጸም ሊያዝ የሚችልው በባንክ ወይም በህግ እንደባንክ በተቆጠሩ ሰዎች ስራ ማስኬጃ ስፍራ ነው፡፡ ከነዚህ ቦታዎች ውጭ ቼክ የተጻፈለት ሰው ክፍያ እንዲፈጸምለት መጠየቅ አይችልም ማለት ነው። አንቀፅ 854 ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል ሰነድ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም ቼክ ልክ እንደ ተላላፊ በብት የሚቋቋም ሰነድ ሆኖ የሚያገለግል ለግብይቱ አላማ ቼኩ ከቀረበ በቼኩ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ወዲያውኑ በቼኩ የተገለጹ ግዴታዎችን መፈጸም አለበት፡፡ በአንቀፅ 855 በቼኩ ላይ ከተፃፈው ቀን አንስቶ በስድስት ወር ውስጥ ለክፍያ መቅረብ እንዳለበት እና እዳ ከፋዩ ወይም ባንኩ በቼኩ ወይም በሚተላለፈው የገንዘብ ሰነድ ውስጥ ያለውን መብት ለአምጪው አልከፍልም ለማለት የሚችለው በሁለቱ የግል ግንኙነት ላይ ተመስርቶ፣ በሰነዱ አፃፃፍ ፎርም አለመሟላት፣ በሰነዱ ላይ በተፃፉት ቃሎች፣ ፊርማ፣ ችሎታ፣ ሰነዱ ሲወጣ ውክልና ስልጣን በተመለከተ ብቻ ተመስርቶ መሆኑን በአንቀፅ 717 ይገልፃል፡፡ በተጨማሪ በአንቀጽ 856 መሰረት ቼኩ ከወጣ በኋላ አውጪው እንዳይከፈል የነገረ ከሆነ ባንኩ በቼኩ የተገለጸውን ዋጋ አልከፍልም ማለት ይችላል፡፡ እዚህ ላይ ብዙ ጊዜ የሚስተዋለው ቼክ በተለያየ ምክንያት በችኮላ ታዞ ስህተት ሲኖርበት እና የሂንኑ አውጪው ከተረዳ ወዲውኑ በተሳሳተው ቼክ አማካይነት ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት እንዲያስቆም ለቼክ አውጪው እድል ለመስጠት ታስቦ የተቀረጸ የህግ አግባብ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ አንድ ቼክ የተጭበረበረ ወይም ህጋዊ ያልሆነ ቼክ ነው የሚያሰኙ እንደ ፊርማን አስመስሎ መፈረም፣ የቼኩ መሰረዝ መደለዝ እና በቂ ስንቅ በባንኩ ውስጥ ሳይኖር ቼክን ፈርሞ መስጠት የመሳሰሉ ሲሆኑ ቼክ እንደ ጥሬ ገንዘብ የሚዘዋወር ሰነድ ከመሆኑ አንፃር የማጭበርበር ወንጀል እንዳይፈፀምበት ህግ ሰፊ ጥበቃ የሚያደርግለት ሰነድ ነው፡፡

## ቼክን በመያዣነት ወይም በዋስትናነት መስጠት ይቻላል?

ቼክን ተጠቅሞ በሚደረጉ ግብይቶች ውስጥ ከሚታዩ ችግሮች መካከል ቼክን ለክፍያ እንደዋስትና ወይም መያዣነት መጠቀም ነው፡፡ እዚህ ላይ ሊታወቅ የሚገባው ቼክ ጥቅሙ እንደገንዘብ የክፍያ ሰነድ ሆኖ እንዲያገለግል በመሆኑ ከአውጪዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነው፡፡ ሆኖም አንዳንድ ሰዎች ቼክን እንደ መያዣነት ወይም እንደዋስትናነት በጊዜያዊነት በመስጠት ተመላሽ ይደረጋል በሚል የሚደረገው መለዋወጥ ከህጉ እውቅና ውጪ በመሆኑ ሊታረም ያስፈልጋል፡፡ ቼክ የክፍያ ሰነድ እንጂ መያዣ ወይም ዋስትና መስጫ አይደለም፡፡ ቼክ ወጪ ተደርጎ ለሰው ከተሰጠ ተከፋዩ እስከ ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለከፋዩ ባንክ አቅርቦ ክፍያ እንዲፈፀምለት ለመጠየቅ ህጉ መብት ይሰጣል፡፡ በውስጥ ስምምንት ተከፋዩ ይህ ሁኔታ ካልተፈፀመ ወይም እንዲህ ካልሆነ ቼኩን ለባንክ አታቀርብም የሚል ስምምነት ቢያደርጉም ህጉ ተከፋዩን ቼኩ እንዲከፈለው የማቅረብ መብቱን አይከለክለውም፡፡ በሌላ በኩልም ቼኩን ስሰጠው በቂ ስንቅ ወይም ገንዘብ እንደሌለው አሳውቄዋለው የሚለውም መከራከሪያ በተመሳሳይ በቂ መከላከያ አይሆንም ምክንያቱም ቼክ ያለቅድመ ሁኔታ እንደክፍያ ሰነድ ህጉ ስለሚቆጥረው ነው፡፡ በ1952 ንግድ ህጉ አንቀጽ 855 መሰረት ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ቅድመ ሁኔታ ያልተደረገበት ትዕዛዝ ሆኖ ለከፋዩ በስድስት ወር ውስጥ እንደቀረበ እንዲከፈል የሚጠበቅ ነው፡፡ ስለዚህ ቼክን በመያዣነት ወይም በዋስትናነት መስጠት ህጋዊ መሰረት የሌለው እና ከወንጀል ተጠያቂነትም ስለማያድን ህብረተሰቡ እንዲህ ካለው አሰራር መጠንቀቅ አለበት፡፡

## ቼክ ከወጣ በኋላ ቼክ ያወጣው ሰው በቼኩ የተገለጸው ክፍያው እንዳይፈጸም ማስቆም ይችላል?

ቼክን በተመለከተ በተግባር ከሚታዩ ችግሮች ውስጥ ክፍያ ይቁም የሚለው አሰራር ነው፡፡ ከላይ እንደገለጽነው በንግድ ህጉ አንቀጽ 856 መሰረት ቼኩ ከወጣ በኋላ አውጪው እንዳይከፈል የነገረ ከሆነ ባንኩ በቼኩ የተገለጸውን ዋጋ አልከፍልም ማለት ይችላል፡፡ ይህ የህጉ ድንጋጌ የራሱ አላማ ያለው ሲሆን ለወንጀል ድርጊት ግን ሽፋን ለመስጠት ታስቦ የተደነገገ አይደለም፡፡ በተግባር የሚታየው ሰዎች ቼክ ወጪ አድርገው ከሰጡ በኋላ በቂ ገንዘብ እንደሌላቸው ሲረዱ ለባንካቸው ክፍያ አቁምልኝ ትእዛዝ የሚሰጡበት ሂደት ነው፡፡

በህጉ መሰረት እና የዚህ ዝርዝር አፈፃፀምን ለመወሰን በብሄራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር SSB/ 64/2016 አንቀጽ 5 እና 6 መሰረት የቼክ ክፍያ ይቁምልኝ ትእዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ቼክ ፓድ ወይም ቅጠል ከጠፋ፣ በማስገደድ ቼኩ እንዲፃፍ ከተደረገና መሰል ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ እንጂ በቂ ስንቅ ማኖር ሳይቻል ሲቀር ክፍያ ቀሪ እንዲሆን ለማድረግ የታሰበ አይደለም፡፡ በዚህም መሰረት ባንኮች ክፍያ ይቁም ትእዛዝ ሊፈፅሙ የሚችሉት ከላይ የተገለጹት የየቼኩ መጥፋት እና መሰል ሁኔታዎች ለመፈጸማቸው ከፖሊስ ማስረጃ በ15 ቀን ውስጥ ማቅረብ ሲቻል ብቻ እንደሆነ መመሪያው ያመለክታል፡፡

## የወንጀል ተጠያቂነት

በኢ.ፌ.ድ.ሪ. የወንጀል ህግ መሰረት በቂ ስንቅ የሌለውን ቼክ አውቆም ሆነ በቸልተኝነት ማውጣት በወንጀል የሚያስጠየቅ ተግባር ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ቼክ አውጪ በቂ ስንቅ ሳይኖረው ያወጣ ወይም ፈርሞ ለተከፋይ የሰጠ እንደሆነ በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በቀላል እስራት አንደነገሩ ከባድነት ደግሞ ከአስር አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና የገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ይህ ወንጀል በቸልተኝነት የተፈጸመ ከሆነ ቅጣቱ በመቀጮ ወይም ከአንድ አመት በማይበልጥ ቀላል አስራት ይሆናል፡፡ አንድ ቼክ ፈራሚ ይህን ህግ ተላልፏል ተብሎ የሚጠየቀው ቼኩን በሚያወጣበት(በሚፈርምበት) ጊዜ ወይም ቼኩ ለባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ እንደሆነ ወይም በቸልተኝነትም ከሆነ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ቼክ እንደ ገንዘብ መክፈያ ሰነድነቱ ሰጪው ወይም አውጪው በሚያወጣበት ጊዜ ወይም ለክፍያ በሚቀርብበት ጊዜ በሂሳቡ በቂ ገንዘብ ያለው መሆኑን አውቆ እንዲያወጣ የሚጠበቅበት በመሆኑ ከፍተኛ ሀላፊነትን የሚጥል ግዴታ አለው፡፡ ከዚህ አንፃር ብሄራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር SSB/ 64/2016 አንቀጽ 4 መሰረት ባንኮች መደበኛ ሂሳብ ወይም የቼክ አካውንት ለደንበኛ በሚከፍቱበት ጊዜ ይህን ሀላፊነት እንዲያስገነዝቡ ግዴታ ይጥላል፡፡ ባለቼክ የሆነ ሰው የቼክ አካውንቱ በራሱም ሆነ በሌላ ምክንያት አካውንቱ ከተዘጋ በኋላ ቼክ ፈርሞ መስጠት የሌለን ነገር እንዳለ በማስመሰል በመግለጽ ተጎጂው እንዲያምነው በማድረጉ በ1996 ዓ.ም. በወጣው ወንጀል ህግ በአንቀጽ 692 መሰረት በማታለል ወንጀል በመፈፀሙ ያስጠይቀዋል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ቼክ ላይ ፊርማውን አኑሮ ለተከፋይ ከሰጠ በቼኩ ላይ

የሚፃፉ ዝርዝር ነገሮች ማለትም ተከፋይም ሆነ የክፍያ መጠን በማንም ቢፃፍ ፊርማው የከፋዩ የራሱ እስከሆነ ድረስ ከተጠያቂነት አያድነውም፡፡

## አስተዳደራዊ ተጠያቂነት

ከወንጀል ሀላፊነት በተጨማሪም በቂ ስንቅ ሳይኖረው ቼክ በሚያወጣ ደንበኛ ላይ በብሄራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SSB/ 64/2016 አንቀጽ 5 መሰረት ተጨማሪ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወሰዱበታል፡፡ በመጀመሪያው ጥፋት አድራጊው በባንኩ የጥቁር መዝገብ ስሙ ይሰፍራል፡፡ ከዚህ መዝገብ ስሙ የሚፋቅለት የተሰጠው ቼክ የተከፈለ ከሆነ እና ለአስራ ሁለት ወራት ተመሳሳይ ጥፋት ካልፈፀመ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ለሁለተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ጥፋት ከፈፀመ አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ ስሙ በጥቁር መዝገብ ይሰፍርና ከዚህ ዝርዝር ስሙ ሊወጣ የሚችለው በቼኩ የተመለከተው መጠን ለተከፋዩ ከተከፈለ እና የመጀመሪያው ቼክ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ ለሀያ አራት ወራት ሶስተኛ ጥፋት ካልፈፀመ ሆኖ ለዚህ ጥፋቱ ግን የቼኩን ገንዘብ መጠን 3% ከብር ሀያ አምስት ሺህ ሳይበልጥ ቅጣት እንዲከፍል ተደረርጎ ይሆናል፡፡ በእያንዳንዱ ጥፋት መረጃው ለብሄራዊ ባንክ ሪፖርት እንዲደረግ ይጠበቃል፡፡ ለሶስተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ጥፋት ከተፈፀመ ባንኩ ይህኑ መዝግቦ የደንበኛውን የቼክ አካውንት ዘግቶ የቼኩን ገንዘብ መጠን የ5% ቅጣት ከብር ሀምሳ ሺህ ሳይበለጥ እንዲከፍል በማድረግ በእጁ ያሉ የቼክ ፓድና ቅጠሎችን ለማስመለስ ጥረት ማድረግ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ ብሄራዊ ባንክም ይህን መረጃ ለሌሎች ባንኮች በመስጠት ግለሰቡ የቼክ አካውንት ተጠቃሚ እንዳይሆን ይደረጋል፡፡ በዚሁ ብሄራዊ ባንክ መመሪያ SSB/ 64/2016 አንቀጽ 8 እንደተገለጸው የተዘጋው ሂሳብ የሚከፈትለት የተፈረሙት ቼኮች የተከፈሉ ለመሆኑ ማረጋገጫ ሲቀርብ ወይም የገንዘብ መጠናቸው በዝግ ተቀምጦ ተከፋዮቹ ካልተገኙ በፈራሚው ወጪ በጋዜጣ እንዲጠሩ ተደርጎ እና ሂሳቡ ከተዘጋ ጊዜ ጀምሮ አንድ አመት ሲያልፈው እንዲሁም ሁለተኛ ተመሳሳይ ጥፋት ላለመፈፀም ግዴታ ሲገባ ነው፡፡

በመሆኑም የቼክ ተጠቃሚዎች ይህን ከግንዛቤ በመክተት ቼክን በአግባቡና በህጋዊ መንገድ ለመጠቀም ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል፡፡